# እንደ ካሮት ቁልቁል

(ከግሀሉ በቀለ ቶሮንቶ)

አገራችን ኢትዮጵያ ታሪኳ ረዥምና አኩሪ ሲሆን በቅኝ ገዥዎች ሳትገዛ እራሷን አስከብራ የኖረች አገር መሆኗ እኛንና አፍሪካውያንን የሚያኮራ ሲሆን የውጭውንም ዓለም ጭምር ያስገረመ ጉዳይ ነው። ታዲያ ይህች ጥንታዊት አገራችን ሥልጣኔዋ እንደ ግብፅና ቻይና የቆየ ሲሆን አሁን ያለችበትን ሁኔታ ስንቃኘው በጣም የሚያሳዛን ነው። ባለፉት 200 ዓመታት ውስጥ ብዙ አገሮች ጥለውን ሄደው፤ ዛሬ እኛ ለማኝ እነሱ መጽዋቾች፤ እኛ ተበዳሪ እነሱ አበዳሪ፤ እኛ ኋላ ቀር እነሱ የሰለጠኑ፤ እኛ መሀይም እነሱ የተማሩ፤ እኛ በጦርነት የምናልቅ እነሱ በሰላም የሚኖሩ መሆናቸው የሚገርምና የሚያሳዝን ሁኔታ ነው።

ያገራችንን ኤኮኖሚ ስንመለከት ዛሬ ደሀ ገበሬዎቻችን እንደድሮው ሁሉ በእጅ ነው የሚያርሱት። ያአገሪቱም የምርት መጠን በጣም ዝቅተኛ በመሆኑ በልመና በሚመጣ የውጭ የምግብ እርዳታ መኖር የግድ ሆኗል። በአገራችን መኪና፤ ስልክ፤ መንገድ፤ ጤና ጣቢያ፤ ትምህርት ቤትና ሌሎች መሠረታዊ መዋቅሮች የሌሉባቸው ብዙ የገጠር መንደሮችና ከተሞች አሉ። ሌላው ቀርቶ ከመቶ አመት በፊት አፄ ሚኒሊክ ካስገቡት ባቡር በኋላ የተዘረጋ አንድም የሀዲድ መስመር በኢትዮጵያ የለም። ከመቶ አመት በፊት በኋላ ቀር ቴክኖሎጂ ባቡር ያስገባን ስዎች አሁን በስለጠነው ጊዜ እንዲህ አይነቱን ስራ እንዳናከናውን አይናችንን የደፈነው ምንድነው? እኔ እንደማምነው መሪዎቻችን ማለትም ጃንሆይ፤ መንግሥቱና ጉደኛው መለስ ብዙ ጊዜያቸውን የሚያጠፉት ሀይላቸውን ለማጠናከርና በሥልጣን ላይ ለመቆየት ሲሉ በፖለቲካው ስራ ላይ በመሆኑ ኤኮኖሚው ተረስቷል ማለት ይቻላል። ዛሬም ማገዶችን ኩበት፤ ቅጠልና እንጨት ሲሆን ኩራዝ እንኳን የሌላቸው ወገኖቻችን በሚሊዮን ይቆጠራሉ። ሕዝባችን ዛሬም ባዶ እግሩን ነው የሚሄደው። መቸ ይሆን የሚያልፍለት?

ፖለቲካውን ደግሞ ካየን መሬት ላራሹ፤ ዴሞክራሲ አሁኑኑ፤ ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋም፤ ብለን የዘውድ አገዛዝ ከተወገደ ወዲህ የእርስበርስ ጦርነትና እልቂት ውስጥ ገብተን የምንበላው ነገር የሌለን ደሀ ሕዝቦች በቡና ሽያጭ፤ በብድር ወይንም በእርዳታ ባገኘነው ገንዘብ የጦር መሳሪያ እየገዛን አገራችን የበለጠ እንድትቆረቁዝ ሆናለች። በደርጉ ዘመን ብዙ ግፍ ተሰረቷል። ሌላው ቀርቶ ዛሬ ስናስበው የ60ዎቹ የኢትዮጵያ የሲቪልና የሚሊተሪ መሪዎች መረሸን የግፍ ግፍ ነው።

የነዚህ ሰዎች ወንጀል ባለመሬት፣ ባለሀብትና ባለስልጣን መሆናቸው እንጂ በሞት የሚያስቀጣ የአገር መክዳት ወንጀል አልነበረባቸውም። ይህን ድርጊት ደግሞ በማወቅም ሆነ ባለማወቅ የተሳተፈበትም ደግሞ በቀይ ሽብር፣ በነጭ ሽብር ወይንም በሌላ ሽብር ተመሳሳይ ፅዎ ቀምሷል። መንግሥታት ተቀያየሩ፣ ሕዝቡም እንደ ልደታ ቆሎ ታመሰ እንጂ የተገኘ ምንም ውጤት የለም። እንዲያውም አጠቃላይ የፖለቲካ፣ የኤኮኖሚና የማህበረሰባዊ እድገታችን እንደ ሸንኮራ አገዳ ወደ ላይ ሳይሆን እንደ ካሮት ቁልቁል ሆኗል ብል ዋሸ አልባልም። ለዚህ ማስረጃ እስታትስቲክስ አላቀርብም ምክንያቱም ሁሉም የሚያውቀው ያገጠጠ ሐቅ ነውና።

ኢትዮጵያ የሰው ልጅ መብት የማይከበርባት፣ ዜጎቿ እንደከብት የሚታሰሩባት፣ የግፍ አገዳደል፣ ድብደባና የስጋት ኑሮ ያለባት ምድር ሆናለች። በተለይም ደግሞ አሁን ያሉት የወያኔ ገዥዎች በሕዝባችን ውስጥ የመከፋፈልና የመጠላላት መርዝ ረጭተው፣ ዓይናቸው በጥቅምና በጠበንጃ ታውሮና ህሊናቸው ከድቷቸው ታሪክ አንድ ቀን ሊያዎርዳቸው እንደሚችል ባለማወቅ ወይንም ባለማመን ፍዳችንን አብዝተውት ይገኛሉ።

የግንቦቱ ምርጫ አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ ወያኔን እንደማይፈልግ ያረጋገጠበት መሆኑን መለስና አጀቦቹ እራሳቸው በልባቸው ጠንቅቀው ያውቁታል። ነገር ግን ጥቅም፣ ሀይልና ሥልጣን ለመከላከል ጠበንጃ በማንሳት የጠላቸውን ሕዝብ በጉልበት ሊገዙት ወስነዎል። ከታሪክ መማር ቢችሉ ምን አለበት? በወቅቱ የታወቁና የተፈሩ መሪዎች --እነ ሂትለር፣ ሞሱሊኒና ስታሊን ዛሬ የሰው ዘር ሁሉ የሚጠላቸው እርኩስ ፍጡራን ናቸው። በተቃራኒው ደግሞ መሀትማ ጋንዲ፣ ማርቲን ሉተር ኪንግና ማንዴላ የሰው ዘር በሙሉ የሚያደንቃቸው ቅዱሳን መሪዎች ናቸው። ይህ እውነታ እነመለስ ሳይገባቸው አይቀርም፡ ነገር ግን አዕምሯቸው በውሸት፣ በቅጥፈት፣ በክህደት፣ በእብሪትና በጥላቻ ስለተሞላ ትክክለኛውን ነገር ለመገንዘብ፣ ለማሰብና ለማስታወስ የሚያስችል ክፍት ቦታ ሊኖረው አልቻለም።

የኢትዮጵያ እስር ቤቶች በፖለቲካ እስረኞች ተሞልተዋል፣ እነዚህ አገር ወዳዶች የተለየ የፖለቲካ አመለካካት፣ ዝንባሌ ወይንም እምነት ስላላቸውና ለወያኔ አገዛዝ ስለማይመቹ መለስና አጀቦቹ በድብደባ፣ በግድያና በእስር ትግሉን የሚያኮላሹ ይመስላቸዎል። “ታጋይ ይሞታል እንጅ ትግል አይሞትም” የሚባለውን አባባል መለስ፣ አዲሱ፣ በረከት፣

ተፈራ፣ መስፍን፣ አባዱላና መሰሎቻቸው ሳያውቁት አይቀርም። ነገር ግን ሆዳቸው ህሊናቸውን አሸንፎ በክህደት ቁልቁለት ወደ አዘቅት ሲንከባለሉ ይገኛሉ። ሥልጣንና ሀይል የሕዝብ መሆኑንና የሰዎችን ፍላጎትና ምርጫ የሚያሸንፍ ምንም ሀይል እንደሌለ በምን ቋንቋ እንንገራቸው። ዳሩ ግን አውቀ የተኛ ቢቀሰቅሱት ስለማይነቃ እነዚህን የጥፋት መልእክተኞች ዲያቢሎስ በተኙበት ያስቀራቸው እላለሁ።

የማህበረሰባችን ችግር ደግሞ በኢትዮጵያ ውስጥ ያለው የፖለቲካና ኤኮኖሚ ይዞታ አንፀባራቂ መስተዋት ነው። ጊዜያቸውን ትምህርት ቤት ማሳለፍ ያለባቸው በብዙ መቶ ሽህ የሚቆጠሩ ወጣት ልጆች በየከተማው መንገድ ሲዋከቡ ይገኛሉ። ይህ በጣም አደገኛ ክስተት ነው፣ የአንድ ህብረተሰብ ጤናማነት የሚለካበት ባሮ ሜትር ወጣቱ ትውልድ ነው። ወጣቱ ላይ ችግር ከታየ ቤተሰብና አገር ተበላሸቷል ማለት ነው። ኤድስ፣ ወባ፣ ቲቢና ሌሎች በቀላሉ ሊድኑ የሚችሉ በሽታዎች የኢትዮጵያውያን ሕዝብ እየጨረሱት ይገኛሉ። ሥራ አጥነት፣ ረሀብ፣ በሽታ፣ መሀይምነት፣ ተሰፋ መቁረጥና ለማኝነት የማይቋራረጡ ሰንሰለቶች ሆነው የኢትዮጵያ ኑሮ ለብዙዎች የሲያል ኑሮ ሆኗል። በትምህርት ጥራት መውደቅና በተዛባ ካሪኩለም ምክንያት ብዙ ተማሪዎች ወጣት ጡረተኛ ሆነው ከቤተሰቦቻቸው ጋር ሲቸገሩ ይገኛሉ። ሴተኛ አዳሪነቱና ሌሎች በባህላችን አስከፊ የሆኑ ተግባሮች ለምሳሌ የወጣት ልጃገረዶች ለገንዘብ አካላቸውን መሸጥ፣ የአደንዛዥ እፆች ፍጆታና የመሳሰሉ ርካሽና አሳፋሪ ተግባሮች ወያኔ የፈጠረው ኤኮኖሚ ዘርፍ ወይም ቅጥያ ሆነዋል ማለት ይቻላል። ወጣት ሴቶቻችን ወደ አረብ አገር እየተጋዙ ዘግናኝ ሁኔታዎች እየተፈፀሙባቸው አንዳንዶቹም ተገለው እሬሳቸው ተመልሶ ይመጣል። አድሎና ሙስና ተንሰራፍቶ ሰብአዊነት ጠፍቶ ኢትዮጵያ ጥቂቶች ህይወታቸውን የሚቀጩባትና አብዛኛው በምሬትና በሰቆቃ የሚኖርባት ሆናለች።

ኢትዮጵያ ውስጥ ፍትህን፣ እኩልነትን፣ ነፃነትና መብትንና የኤኮኖሚ ብልፅግናን ማምጣት የሚቻለው የአገሪቱ የፖለቲካ አስተዳደር ሲስተካከል ብቻ ነው። ማንኛውም አገራዊ ሆነ ብሄረሰባዊ ችግር የሚፈታው በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩትን ሕዝቦች ሁሉ መወከል የሚችል ትክክለኛ አስተዳደር ሲኖር ብቻ ነው። ዘረኝነት፣ ጠባብነትና ጎጠኝነት ለኢትዮጵያ ሕዝብ አይስማሙም። የኢትዮጵያ ሕዝብ እንደሠርገኛ ጤፍ ነው፣ ሊለያይ አይችልም። በስራ፣ በትምህርት፣ በኑሮ፣ በትዳር ሀይማኖትና ዘር ሳንለይ ለረዥም ዘመናት አብረን የኖርን ነን። ችግራችን፣ ፍላጎታችን፣ ጥያቂያችን አንድና ተመሳሳይ

ነው። ከሁሉም በላይ ደግሞ እርስ በእርስ የሚያጫርሰን ደህነታችን ነው። ደሀ ሕዝብ ለመኖር የሚያደርገውን ትግል መጥፎ የፖለቲካ መሪዎች ለራሳቸው ዓላማ ማራማጃ የደርጉትና ገንዘብንና የተፈጥሮ ሀብትን ይቆጣጠሩበታል። የሚደግፋቸው የጥቅማቸው ተካፋይ ሊሆን ሲችል የሚቃወማቸው ደግሞ አሳሩን ይበላል። ለዚህ ነው ለሕዝብ የሚሰሩ መሪዎች የሚያስፈልጉን። ጥሩ መሪዎች የፖለቲካ ራእይ፤ የሕዝብ ፍቅርና አክብሮት፤ የሥራ ጥራትና ትጋት አላቸው። በኛ አገር አምባገነን መሪዎች እየተነሱ ምድራችንን ቀውጢ እያደረጎት የታሪክን ጎማ በኋላ ማርሽ ሲያሽከረከሩት ይገኛሉ።

ከሁሉም በላይ እንደወየኔ አይነት መጥፎ አገዛዝ ኢትዮጵያ ውስጥ መጥቶ አያውቀም። ወያኔ ለሚገዛው አገር ለኢትዮጵያ ጠላት የሆነ ቡድን ነው። ለዚህ በቂ ማስረጃ የሚሆኑት የኤርትራ መገንጠል፤ የአሰብ ወደባችንን ማጣት፤ የባድመ ጦርነትና የብዙ ሽህ ለውጥ ፈላጊ ኢትዮጵያውያን በእሰር ቤት መታጎርና መሞት ነው። የትግራይን ምድር ነፃ እናወጣለን ብለው የተነሱ ሰዎች ታላቂ ኢትዮጵያ በሯ ክፍት ሆኖ ስላገኙት ዘው ብለው ገብተው ዛሬ እነሱ ኗሪ እኛ ደባልና ስደተኛ ሆነናል። አብዛኛው የትግራይ ሕዝብ ታሪክ እንደሚያሳየው ኢትዮጵያን ጠብቆና ባዕድ ወራሪዎችን መክቶ ከመኖሩም በላይ በባህሉ፤ በሀይማኖቱና ባጠቃላይ አመለካከቱ ኢትዮጵያዊ ሆኖ የኖረ ነው። ዛሬ ግን የወያኔ መሪዎች አፍነውትና የውሸት ተስፋና ጉራ እየመገቡት ከሌላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር ሊያቃቅሩት ይፈልጋሉ። ይህ ግን አይሳካም። ሕዝብ ያያል፤ ሕዝብ ይገነዘባል፤ ሕዝብ የሚበጀውንና የማይበጀውን ያውቃል፤ ሕዝብ ይፈርዳል። ይህ የታወቀና ሊጠፋ የማይችል የሰው ልጅ የስነልቦና መሠረት ነው። በመሆኑም ሕዝብ ነፃ እስኪሆን ድረስ ሠላም አይኖረውም። ችግር አይለቀውም። ማንኛውም ህብረተሰብ ጉዞው ነፃነትና ዴሞክረሲ ፍለጋ ነው። የጊዜ ጉዳይ ነው እንጂ እዚያ ቦታ የማይደርስ አይኖርም። እኛም በአገራችን የተጓዝነው መንገድ 31 ዓመት የፈጀብን ሲሆን ገና እዚያ አልደረስንም። መድረሳችን ግን አይቀርም። የሰው ልጆች ትግልን ሊያፋጥኑት ወይንም ሊያንቀረፍፉት ይችላሉ እንጂ የሚሆንን ነገር ከመሆን ሊያስቆሙት አይችሉም። ስለዚህ ወገኖቼ አበሾች ሆይ! ወደ ኋላ ታሪካችሁን እያያችሁ፤ አሁን ያላችሁበትን ሁኔታ እየገመገማችሁና ወደፊት ማድረግ ያለባችሁን እያቀዳችሁ የትግላችሁን ጉዞ ቀጥሉ። ውድቀታችንም ሆነ ስኬታማችን፤ ደስታውም ሆነ ሀዘኑ፤ ደህነትም ሆነ ብልፅግና፤ ኩነኔም ሆነ ቅድስና ሁሉም የኛ ታሪክ ነው፤ አስረናል ታስረናል፤ ገለናል ሞተናል፤ ተሰደናል አሰድደናል፤

የፈረንሳይ ወይም የጀርመን ጦር አልወረረንም። ሁሉም ነገር እኛው በኛ ነው። አገራችንን የምናጠፋውም ሆነ የምናለማውም እኛ ነን። ከሀዲዎችን፤ ቅጥረኞችን፡ ፋሽስቶችንና የአገር ጠላቶች ታግልን በማሸነፍ ኢትዮጵያን ለኢትዮጵያውያን መመለስ አለብን።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ! በግንቦቱ ምርጫ ፍላጎታችሁ ታውቋል ነገር ግን ውጤቱ ተሰርቋል። ወያኔ በቃኝ ብላችኋል ነገር ግን ታፍናችኋል፤ ታስራችኋል፤ ተደብድባችኋል፤ ታፍሳችኋል፤ ተገላችኋል። ይሁን እንጂ አገራችን ኢትዮጵያ ከለማኝነት ወደ መጽዎችነት፤ ከኋላ ቀርነት ወደ ሥልጣኔ፤ ከአምባገነንነት ወደ ነፃነት፤ ከአድሎ ሥራ ወደ እኩልነት እስክትሸጋገር ድረስ ትግላችን ስለሚቀጥል አይዞን!

ኢትዮጵያችን የምታኮራ አገር ናት። እኛ የሰው ዘር፤ የቋንቋ፤ የሀይማኖት፤ የባህልና የታሪክ ሙዚየም ነን። ታላቅ አገርና ታላቅ ሕዝቦች ነን። አመራር ነው ችግራችን እንጂ ሌላ ነገር አይደለም። በመሆኑም ጊዜያችሁ፤ ጉልበታችሁ፤ ገንዘባችሁና፤ ጥበባችሁ ትክክለኛ አመራር ምሥርታ ላይ ያተኩር! እዚያች ምድር ላይ መፈጠራችን በጣም የሚያኮራና በባይተዋሮች ዕድለኞች የሚያሰኘን ቀን እሩቅ አይሆንም።

ሠላም፤ ፍቅርና ነፃነት ለኢትዮጵያ
አይዞን!